אוניברסיטת חיפה
UNIVERSITY OF HAIFA
جامعة حيفا

התנועה לחופש המידע (ע"ר)
الحركة لحرية المعلومات
The Movement for Freedom of Information

# ኮምፒዩቴሩ በእኔ ላይ እንደዚህ የወሰነው ለምንድን ነው?

### ስለ አልጎሪዝም ግልጽነት አስፈላጊነትና ጉዳት ከደረሰብዎት ምን ማድረግ እንደሚቻል

## አልጎሪዝም ምንድን ነው?

በቀላል አነጋገር አልጎሪዝም ማለት ቀመር ("ኑስሐ") ማለት ነው። በሌላ አነጋገር ኮምፒዩቴር አውቶማቲክ በሆነ መንገድ እንዲተገብረው የሚሰጡት ተከታታይ ትእዛዞች ናቸው። ኮምፒዩቴሩን የሚያሠራው የሚሰጠው አልጎሪዝም ሲሆን ይህም ኮምፒዩቴሩ ወደተወሰነ ውጤት እንዲያመራ ያደርገዋል።

**መደበኛ አልጎሪዝም ምን እንደሆነ ለማብራራት የቢቱዋሕ ሌኡምን ድረ ገጽ እንደ ምሳሌ አድርገን እንውሰድ።** ድረ ገጹ አልጎሪዝምን በመጠቀም ዋስትና ያለው ሰው የሥራ አጥነት ተቆራጭ ማግኘት ይችል እንደሆነ ስሌት ያደርጋል። **ይህንን እንዴት ነው የሚያከናውነው?** ባለዋስትናው ዝርዝር መረጃዎቹን በኦንላይን ቅጽ ("ቶፌስ መኹቫን") ውስጥ ያስገባል። ከዚያም አልጎሪዝም መረጃዎቹን በማቀናበር ባለዋስትናው የሥራ አጥነት ተቆራጭ ማግኘት ይችል ወይም አይችል እንደሆነ የመጨረሻውን መልስ ይሰጣል።

## አልጎሪዝም ምን እንደሆነ ማወቅ ለምን አስፈላጊ ነው?

ዛሬ የምናደርጋቸው አብዛኛዎቹ ክንውኖች በተለይም ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር የምናደርገው ግንኙነት የሚተገበሩትና የሚቀናበሩት በአልጎሪዝም አማካይነት ነው። አንዳንዴም ሰዎች ጣልቃ ሳይገቡበት ነው። ይህም ማለት ውሳኔዎች የሚደረጉት የሰው ልጅ ቁጥጥር ሳይደረግበት ነው።

ከእነዚህም ውስጥ አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ለቢቱዋሕ ሌኡሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች፣ የአርኖና ክፍያዎች፣ በሥራ ሚኒስቴር የሥራ ሁኔታን መመዝገብ፣ በትራንስፖርት ሚኒስቴር ድረ-ገጽ ላይ የመኪና ፈቃድን ማሳደስ፣ በታክስ ባለሥልጣን ድረ-ገጽ ላይ የግብር ሪፖርት ማቅረብ፣ ወዘተ. ናቸው።

**አልጎሪዝምን መጠቀም ብዙ ጥቅሞች ያስገኛል**። አልጎሪዝም 24 ሰዓት ሙሉ የሚሠራ ሲሆን ግብአቶችን ቶሎ የማብላላት ዓቅም አለው። ግብአቶችን ከተለያዩ የመረጃ ቋቶች ጋር ወዲያውኑ ለማጣመርም (ለምሳሌ የመታወቂያ ወረቀቱን ቁጥር ከግለሰቡ ስም ጋር ለማነጻጸር) ይረዳል። አልጎሪዝምን መጠቀም ለዜጋ የሚሰጠውን አገልግሎት ያቀላጥፋል፣ የሰው ጉልበት ይቆጥባል፣ እንደዚሁም ለመጠበቅ የሚወስደውን ጊዜም ያሳጥራል። እንደዚሁም የተለያዩ ጉዳዮችን በተጓዳኝ ያከናውናል። ሌላው ጥቅም ደግሞ አልጎሪዝም አያዳላም እንደዚሁም እንደ ሰው አይሳሳትም።

## እንደዚያ ከሆነ ችግሩ ምንድን ነው?

ችግሩ **አልጎሪዝም በተፈጥሮው ግልጽ አይደለም** ማለትም ለሰፊው ሕዝብ በግልጽ የቀረበ አይደለም። መንግሥታዊ የሆኑ ድረ ገጾችን የሚጠቀሙ ሰዎች አልጎሪዝም እንዴት እንደሚሠራ አያውቁም። **ይህ ከምን ጋር ይመሳሰላል?** እስቲ የግብር ባለሥልጣን ሠራተኛ ከወትሮው እጥፍ የገቢ ግብር ተመን ለምን እንደተመነብዎት ሊገልጽልዎት ያልፈለገበትን ሁኔታ አስቡት።

ነገር ግን ሰው ሠራሽ አስተሳሰብ ("ቢና ሜላኹቲት") ወደ ሕይወታችን በሚገባበት ጊዜ ነገሮች እየተባባሱ ይሄዳሉ። መደበኛ አልጎሪዝምን በሚመለከት ምን ዓይነት ቀመር እንደሚጠቀም ማወቅ የሚቻል ሲሆን ሰው ሠራሽ አስተሳሰብን በሚመለከት ግን ውጤቱ እንዴት እንደተገኘ እስከ መጨረሻ ማብራራት አይቻልም። በሌላ አነጋገር ሰው ሠራሽ አስተሳሰብ ነገሮችን የሚማርበት መንገድ ወደ መጨረሻው ውጤት እንዴት እንደደረሰ ለማወቅ አያስችልም። በመሆኑም ሰው ሠራሽ አስተሳሰብ የተገነባበት ግልጽ መንገድ በጣም አስፈላጊ ነው።

## ስለሆነም ምን ማድረግ ይቻላል?

**በመጀመሪያ ኮምፒዩቴር ሊሳሳት እንደሚችል ማወቅ ያስፈልጋል።** ምክንያቱም ከላይ ባለው ክፍል የሰው ልጅ ሊሳሳት እንደሚችል ጠቅሰን ነበር። ይህ እንደዚያ ከሆነ አልጎሪዝሞች ደግሞ የሚቀናበሩት በሰው ልጆች አማካይነት ነው። በመሆኑም ሁልጊዜ ስሕተቶች የሚጠበቁ ሲሆን በተለይም አልጎሪዝሞች በሚዘጋጁበት ጊዜ። አብዛኛውን ጊዜ "ኮምፒዩቴር አይሳሳትም" ተብሎ የሚሰጠው መልስ ትክክል አይደለም። ይህም መልስ ትክክል የማይሆነው ሰው ሠራሽ አስተሳሰብን በተመለከተም ጭምር ነው። ምክንያቱም ሰው ሠራሽ አስተሳሰብን መጠቀም አልጎሪዝሙ የሚያዳላ፣ አግላይ ወይም አሳሳች ነገሮችን እንዲማር ሊያደርግ ስለሚችል ነው።

**እኔ ላይ ምን እንደተወሰነ ማወቅ እፈልጋለሁ። ይህንን የማውቅበት መንገድ አለ ወይ?**

**መልሱ አዎን ነው!**

1

የተለያዩ ሕዝባዊ አስተዳደሮች አንድ ነገር እንዴት እንደተወሰነ ምክንያታዊ ማብራሪያ የመስጠት ግዴታ አለባቸው። እያንዳንዱ ግለሰብ ስለእሱ የተሰጠውን የውሳኔ ማብራሪያ ከመንግሥት ሠራተኞች የመቀበል መብት አለው።

ውሳኔው እንዴት እንደተሰጠ ምክንያቶቹ እንዲብራሩ በመንግሥታዊ ድረ-ገጽ ወይም በጥሪ ማእከል በኩል ማመልከት ይቻላል። የመንግሥት ሠራተኛውም ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በ 45 ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት። እምቢ ካለ ወይም 45 ቀናት ካለፉ፣ ለዚያ የመንግሥት ቢሮ ወይም ባለሥልጣን ይግባኝ የማቅረብ አማራጭ አለዎት። ይህ መብትዎ ነው፣ እንዳይተው!

2

በመረጃ ቋቶች ውስጥ ስለእርስዎ ስለተሰበሰቡ መረጃዎች ምን እንደሆኑ ለማወቅ መረጃ የመቀበል መብት አለዎት። እያንዳንዱ ሰው በራሱ ወይም በጠበቃው አማካይነት በመረጃ ቋቶች ውስጥ ስለእርሱ የተሰበሰበውን መረጃ የማየት መብት አለው። ምናልባም በዚህ ዓይነት መንገድት ስሕተቱን ማጣራት ይቻላል።

3

በተጨማሪም የመረጃ ነፃነት ሕግ አንድ ሰው ስለራሱ መረጃ እንዲቀበል ያስችለዋል። እንደዚሁም ነጻ መረጃ ከቀረጥ ነጻ ነው። በመሆኑም ስለዚህ የመረጃ ጥያቄን ለሚመለከተው ባለሥልጣን (በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ውስጥ መረጃን በሚመለከት ለተሾመው) በመላክ ስለእርስዎ ያሉትን መረጃዎች ለመቀበል መጠየቅ ይችላሉ።

## እኔን በቀጥታ ስለማይመለከት ማረጃ ምን ማድረግ እችላለሁ?

ማንኛውም ዜጋ ወይም ኗሪ መረጃ የማግኘት መብት አለው። በመረጃ ነፃነት ሕግ መሠረት ማንኛውም የእስራኤል ዜጋ ወይም ኗሪ በቀጥታ ከእሱ ጋር ግንኙነት በሌላቸው ጉዳዮችም ላይ ቢሆን ማንኛውንም መረጃ ከመንግሥት ባለሥልጣን የማግኘት መብት አለው። ይህ በመንግሥት ላይ ትችት የሚሰነዝርበት ዘዴ ነው። ማንኛውም የመንግሥት ባለሥልጣን በመረጃ ነፃነት ሕጉ እንደተገለጸው የመረጃ ነፃነት ሕግን የማስፈጸም ኀላፊነት ያለው ሲሆን ባለሥልጣኑ የመረጃ ጥያቄን በተመለከተ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል። ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ፣ በፍትሕ ሚኒስቴር ውስጥ የመረጃ ነፃነት ለማግኘት በመንግሥት ክፍል ድረ-ገጽ ላይ ባለው የማመልከቻ ቅጽ በኩል ማመልከት ይችላሉ።

በዚህ ረገድ እስካሁን ድረስ ፍርድ ቤቱ የመረጃ ነፃነት ሕግ በአልጎሪዝም አጠቃቀም ላይ ተፈፃሚነት እንዳለው በማያሻማ መልኩ ውሳኔ አለመስጠቱን እናስታውቃለን (<u>የመረጃ ነፃነት ጥያቄን የማቅረብ መመሪያ ተያይዞ ቀርቧል</u>)።

የሕግ፣ ቴክኖሎጂ እና ሳይበር ክሊኒክ፣
የሕግ ፋኩልቲ፣ ሐይፋ ዩኒቨርሲቲ
Cyber.Clinic@law.haifa.ac.il

የመረጃ ነፃነት ንቅናቄ
foi@meida.org.il

במימון משותף של
האיחוד האירופי

פרסום זה נתמך ע"י מימון האיחוד האירופי.
תכני הפרסום הם תחת אחריותן הבלעדית של הקליניקה למשפט, טכנולוגיה וסייבר והתנועה לחופש המידע, ואינם משקפים בהכרח את עמדות האיחוד האירופי.